# ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የሚያጋልጡ የታሸጉ ምግቦችን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁ....../2018

ጤናማ ምግብና አመጋገብ ጤናን ለመጠበቅ በተለይም ከአመጋገብ ጋር በተያያዘ ተላላፊ ላልሆኑ ህመሞች የሚኖረውን ተጋላጭንት በማስቀረት ጤናማና ምርታማ ዜጋን ለማፍራት ከፍተኛ አስተዋጽዎ የሚያበረክት መሆኑን በመገንዘብ፤

በኢትዮጵያ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እየጨመሩ በመምጣታቸው ህብረተሰቡን ለጤና፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በማጋለጥ፤ ሀገሪቱን ለመድኃኒት አቅርቦትና ህክምና አገልግሎት ከፍተኛ ወጪ በመዳረግ ዘርፈ-ብዙ ጉዳቶችን እያደረሱ በመሆኑ፤

ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ምክንያት የሚደርሱ ሕመሞችና ሞቶችን በመከላከልና በመቀነስ፤ የዜጎችን ጤንነት የማሻሻል የአገሪቱ የጤና ፖሊሲ ዋና ዓላማ በመሆኑ በአመጋገብ ሁኔታ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች አጋላጭ የሆኑ በፋብሪካ ሂደት የተለወጠ ስብ (ትራንስ ፋት) ያለው፤ በከፊል የሀይድሮጂኔሽን ሂደት ያለፈ እንዲሁም ከመጠን ያለፈ ጨው፣ ስኳር የያዙ ምግቦችን መቆጣጠር ለፖሊሲው ትግበራ ዓይነተኛ ሚና ያላቸው በመሆኑ፤

በፋብሪካ ተዘጋጅተው ለህብረተሰብ የሚቀርቡ የምግብ ምርቶች በውስጣቸው ያለውን የምግብ ንጥረ ነገር ይዘትና መጠን በግልጽ በምግቡ ማሸጊያ ላይ እንዲቀመጥ እንዲሁም ቁጥጥር የሚደረግባቸውን የምግብ ንጥረ ነገሮች ከመጠን በላይ የያዙ ሲሆን የጤና ማስጠንቀቂያ ጭምር እንዲይዙ በማድረግ ህብረተሰቡ ስለምግቡ ምንነት መረጃ እንዲኖረው በማስቻል የዜጎችን መረጃ የማግኘት እና ጤናማ ህይወት የመኖር መብት መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 55 ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ ``ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የሚያጋልጡ የታሸጉ ምግቦችን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁ....../2018`` ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) **"ምግብ"** ማለት በፋብሪካ ተመርቶ እና ታሽጎ ለሰው ምግብነት የሚውል ነገር ሲሆን ገበያ ላይ የዋለ ወይም ለኀብረተሰብ አገልግሎት የቀረቡ ዕጽዋት፣ የዕጽዋት ውጤት፣ የእንስሳት እና የእንስሳት ተዋጽኦ፣ የምግብ ጨው፣ ውኃ ወይም ሌላ መጠጥ ወይም ምግብ ለማምረት ወይም ለማከም የሚውሉ ማንኛውንም ንጥረ-ነገሮች የሚያካትት ነው፤
2) **"ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብ ንጥረ ነገር"** ማለት በምግብ የንጥረ-ነገር መለያ ሞዴል ከተቀመጠው መጠን በላይ በምግብ ውስጥ የሚገኝ ለምግብነት የሚውል ጨው፣ ስኳር፣ ሳቹሬትድ ስብ፣ ወይም በፋብሪካ ሂደት የተለወጠ ስብ፣ ሲሆን በማንኛውም መጠን ያለ ስኳር ያልሆነ ማጣፈጫ፣ እና ሌላ በባለስልጣኑ የሚወሰን የምግብ ንጥረ ነገርን ይጨምራል፤
3) **"የምግብ ንጥረ-ነገር መለያ ሞዴል"** ማለት ሳይንስን መሰረት በማድረግ በሽታን መከላከል ወይም ጤናን ማበልጸግ ጋር በተያያዘ ምግብን ባለው የንጥረ ነገር ስብጥር ወይም መጠን መሰረት የሚመደብበት ሰነድ ነው፤

4) **"ከመጠን ያለፈ"** ማለት በአንድ ምግብ ውስጥ ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብ ንጥረ ነገር በምግብ ንጥረ-ነገር መለያ ሞዴል ከተቀመጠው መጠን አንጻር "ከመጠን ያለፈ" በሚለው ደረጃ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ነው፤

5) **"ስብ"** ማለት ጠጣር ወይም ከፊል ጠጣር ንጥረ-ምግብ ሆኖ በውስጡ ፎስፎሊፒድ፣ ሊፒድ፣ ግላይስራይድ እና ፎስፈፋታይድ ንጥረ ነገሮችን የያዘ ከእንስሳት ወይም ከእጽዋት የሚገኝ ንጥረ ነገር ነው፤

6) **"በፋብሪካ የምርት ሂደት የተለወጠ ስብ"** ማለት በፋብሪካ በተመረተ ምግብ ውስጥ የሚገኝ በሃይድሮጅኔሽን፣ በማቀነባበር ወይም በማጣራት ሂደት የተፈጠረ ወይም የተዋሃደ ሊኖሌይክ አሲድን ጨምሮ በለዉጥ ውቅር ውስጥ ድርብ ትስስር ያለው ማንኛውም የስብ አሲድ ሲሆን በቀጥታ ከእጽዋት ወይም እንስሳት ምንጭ የሚገኝ ምርትን አያካትትም፤

7) **"ሳቹሬትድ ስብ"** ማለት በመደበኛ የሙቀት መጠን ዉስጥ የጠጣርነት ባህሪ ያለዉ እና ለጤና የማይስማሙ የኬሚካል ዉህዶችን የያዘ ከእንስሳት ወይም ከእጽዋት ተዋጽኦ የሚገኝ ስብ፣ቅባት ወይም ዘይት ነው፤

8) **"አጠቃላይ ስብ"** ማለት ሳቹሬትድ ስብ፣ እና የተለወጠ ስብ ጨምሮ በምግብ ዉስጥ የሚገኝ ማንኛዉም የስብ አይነት ነው፤

9) **"ጨዉ"** ማለት ለምግብነት የሚዉል የሶዲየም እና ክሎሪን ዉህድ ወይም ሶዲየም ብቻዉን ሲገኝ ነው፤

10) **"ስኳር"** ማለት ምግቡ በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚጨመር ሱክሮስ፣ ፍሩክቶስ ወይም ግሉኮስ የያዘ ጣፋጭ ጣእም ያለዉ ክሪስታል የካርቦሀይድሬት አይነት ነው፤

11) "ስኳር ያልሆነ ማጣፈጫ" ማለት...

12) **"ገላጭ ጽሁፍ"** ማለት በምግብ ተቀዳሚ ማሸጊያ ወይም መጠቅለያ ላይ የሚጻፍ፣ የሚታተም ወይም የሚለጠፍ ስዕል፣ ጽሑፍ፣ ወይም ምልክት ሆኖ በማሸጊያ ውስጥ በአባሪነት የሚከተትን ጽሑፍን ይጨምራል፤

13) ***የማሸጊያ ፊት ገጽ ገላጭ ጽሁፍ "*** ማለት ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብ ንጥረ ነገር በምግቡ ተቀዳሚ ማሸጊያ ወይም እንዳግባበነቱ ሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ማሸጊያ የጤና ማስጠንቀቂያ የሚቀመጥበት ገላጭ ጽሁፍ ነው።

14) **"ተቀዳሚ ማሸጊያ"** ማለት ለተጠቃሚ የሚደርስ ምርትን በቀጥታ የሚነካዉ እና ምርቱን ለመጠቅለል ወይም ለማሸግ የሚዉል ማሸጊያ ነው፤

15) **"የጤና ማስጠንቀቂያ ምልክት"** ማለት በምግብ ማሸጊያው ፊት ለፊት ገጽ ዋና ቦታ ላይ በምግብ ንጥረ ነገር መለያ ሞዴል አንጻር አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ-ምግብ ከመጠን በላይ የያዘ ስለመሆኑ የሚያስጠነቅቅ ግራፊክ ምልክት ነው፤

16) **"ቢልቦርድ"** ማለት ተነጻጻሪ በሆነ ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ በመጠቀም የሚቀርብ የማስታወቂያ መንገድን ጨምሮ በማንኛውም ህንጻ የውጭ ግርግዳ ላይ፣ በህንጻው ሌላ የውጭ ክፍል ላይ ወይም በራሱ በቆመ ማንኛውም መዋቅር ላይ ምርትን ለማስተዋወቅ የሚያገለግል የማስታወቂያ መንገድ ሆኖ በማንኛውም የምግብ ማከፋፋያ ወይም ችርቻሮ ተቋማት ላይ በተሰማሩ ወይም የምግብ አገልግሎት ለህብረተሰብ በሚያቀርብ ድርጅት ቤት ወይም ህንጻ ላይ የተቋሙን ስያሜ ለመግለጽ ሲባል በአባሪነት የሚሰቀል ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ምግብ ምልክት ወይም መለያ የያዘ፣ በህዝብ ማጓጓዣ ትራንስፖርት ላይ የሚለጠፍ ማስታወቂያን ያካትታል፤

17) **"ማህበራዊ ሚዲያ"** ማለት ሰዎች መልዕክት ለመለዋወጥ፣ ለማስተላለፍ፤ ትስስር ለማዳበር፤ ሀሳብ ለመጋራት የሚጠቀሙበት በኢንተርኔት አማካኝነት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች መረጃ የሚደርስበት፣ ወይም ማህበራዊ መስተጋብር የሚስተናገድበት መንገድ ሲሆን የበይነ መረብ መገናኛ ብዙሃንን ያካትታል፤

18)**"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 የተዘረዘሩትን እና የተቋቋሙ ክልሎች የሚያመለክት ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ያጠቃልላል፤

19)**"ባለስልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ምግብ እና መድኃኒት ባለስልጣን ነው፤

20)**"የክልል ጤና ተቆጣጣሪ"** ማለት ይህን አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጡ ህጎችን በክልል ደረጃ ለማስፈጸም ስልጣን የተሰጠዉ የክልል መንግስት አካል ነው፤

21)**"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

22)ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ አገላለጽ ሴትንም ጾታ ይጨምራል።

### 3. የተፈጻሚነት ወሰን

1) ይህ አዋጅ ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ በሀገር ዉስጥ ተመርቶም ሆነ ከዉጭ ሀገር ወደ ሀገር ዉስጥ በሚገባ ለንግድ ወይም በማንኛዉም ሌላ መንገድ ለህብረተሰብ በሚቀርብ ምግብ ላይበመላ አገሪቱ ተፈጻሚ ይሆናል።የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ቢኖርም በዚህ አዋጅ ስለምግብ ንጥረ ነገር መግለጫ የተመለከተው ድንጋጌ በማንኛዉም በሀገር ዉስጥ ተመርቶም ሆነ ከዉጭ ሀገር ወደ ሀገር ዉስጥ በሚገባ ምግብ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ለአልኮል መጠጦች፣ ጥሬ ዕቃ፣ ለህክምና አገልግሎት የሚዉል ምግብ፣ ማሟያ ምግብ፣ የጨቅላ ህጻን እና የህጻን ምግብ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም **"የህጻን ምግብ"** ማለት አግባብ ባለዉ ደረጃ መሰረት ከእንስሳት ወይም ከእጽዋት ተዋጽኦ በፋብሪካ የሚመረት ምግብ ሆኖ እድሜአቸዉ ከ6 ወር እስከ 3 አመት ለሆኑ ህጻናት ምግብነት በፋብሪካ ደረጃ የሚዘጋጅ ሲሆን፤ **"የጨቅላ ህጻን ምግብ"** ማለት እስከ 6 ወር እድሜ ላሉ ጨቅላ ህጻናት መደበኛ የምግብ ፍላጎታቸዉን ለማሟላት አግባብ ባለዉ ደረጃ መሰረት በፋብሪካ የሚዘጋጅ ምግብ ነው፤

## ክፍል ሁለት

## ቁጥጥር ስለሚደረግባቸው የምግብ ንጥረ-ነገሮች

### 4. ጠቅላላ

1) ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ማንኛውም ምግብ አምራች፣አስመጪ፣አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ህጎች መሰረት የሚጠየቁ መስፈርቶችን ማሟላትና ገደቦችን ማክበር አለበት።

2) በማንኛውም መጠን በከፊል ሐይድሮጅኔሽን ሂደት የተለወጠ ስብ የያዘን ምግብ ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ ወይም ለምግብ አገልግሎት ማቅረብ የተከለከለ ነው።

3) በአንድ ምግብ ውስጥ ካለው ከአጠቃላይ ስብ መጠን 2 ግራም ወይም ከዛ በላይ በፋብሪካ የምርት ሂደት የተለወጠ ስብን የያዘ ምግብን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ ወይም ለአገልግሎት ማቅረብ የተከለከለ ነው።

4) ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) አፈጻጸም የስብ መጠን የሚሰላው በምግብ ዉስጥ የሚገኝ በፋብሪካ ምርት ሂደት የተለወጠ ስብ ክብደትን በምግቡ ውስጡ ላለው አጠቃላይ ስብ መጠን በ100 ግራም ስሌት በመቀየር ከመቶ የሚገኘው መጠን ይሆናል።

## 5. ስለምግብ ንጥረ ነገር መለያ ሞዴል

1) በተዘጋጀው የምግብ ንጥረ ነገር መለያ ሞዴል መሰረት  በአንድ ምግብ ውስጥ በሚከተለው መጠን ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብ ንጥረ-ነገር  ከተገኘ ምግቡ ከመጠን ያለፈ ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ-ነገር እንዳለዉ ተቆጥሮ አዋጁ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
   ሀ) በምግቡ ዉስጥ ያለው የሶዲየም መጠን በሚሊግራም ከአጠቃላይ ሃይል መጠን (ኪሎ ካሎሪ) ጋር እኩል ወይም የሚበልጥ ንጽጽር ያለዉ ከሆነ፤
   ለ) ምግቡ ጠጣር ምግብ እንደሆነ ምግቡ ዉስጥ ከሚገኝ አጠቃላይ ኃይል 10% ያክል ወይም የበለጠ ከስኳር የሚመነጭ ኃይል መጠን ካለው፤
   ሐ) ምግቡ በስኳር የጣፈጠ ፈሳሽ እንደሆነ ምግብ ውስጥ ከሚገኝ አጠቃላይ ኃይል 5% ያክል ወይም የበለጠ ከስኳር የሚመነጭ ኃይል መጠን ካለው፤ ወይም
   መ) ምግቡ ከሚሰጠው አጠቃላይ ኃይል ዉስጥ 10% ወይም ከዚያ በላይ ኃይል ከሳቹሬትድ ስብ የሚገኝ እንደሆነ፤ ነው፡፡
2) ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 (ለ) እና (ሐ) አፈጻጸም አንድ ግራም ስኳር አራት ኪሎ ካሎሪ ሃይል እንደሚሰጥ ይቆጠራል፡፡
3) ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(መ) አፈጻጸም አንድ ግራም ሳቹሬትድ ስብ ዘጠኝ ኪሎ ካሎሪ ሃይል እንደሚሰጥ ይቆጠራል፡፡
4) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተግባራዊ የሚደረገዉ በአንድ ነጠላ ምግብ የተጣራ ክብደቱን መሰረት በማድረግ በ100 ግራም ወይም 100 ሚሊ ሊትር ውስጥ ያለውን ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ-ነገር መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡
5) ማንኛዉም የታሸገ ምግብ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በምግብ ማሸጊያ ላይ አምራቹ ባስቀመጠዉ መመሪያ መሰረት ተጨማሪ መዋሃድ የሚፈልግ ከሆነ የሚዋሃድበትን ነገር መጠን ከግምት በማስገባት በ100 ግራም ወይም ሚሊ ሊትር ምርት ላይ ተመስርቶ ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብ ንጥረ ነገሩ መጠን መሰላት ይኖርበታል፡፡
6) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆኖ ተጨማሪ የምግብ ንጥረ-ነገር ላይ መጠን ማስቀመጥ ያስፈለገ እንደሆነ የምግብ ንጥረ-ነገር መለያ ሞዴልን መሰረት በማድረግ የምግብ ንጥረ-ነገሩን ከመጠን ያለፈ ሊያስብለው የሚችለውን መጠን በመመሪያ ባለስልጣኑ ሊወስን ይችላል፡፡

## 6. ገላጭ ጽሁፍ

1) ማንኛውም  ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ምግብ በምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 እና ማስፈጸሚያ ህጎቹ መሰረት ገላጭ ጽሑፍ መያዝ አለበት፡፡
2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ምግብ ገላጭ ጽሑፍ በዚህ አዋጅ የተቀመጡ ተጨማሪ የገላጭ ጽሑፍ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡
3) ማንኛውም በፋብሪካ የሃይድሮጅኔሽን ሂደት ያለፈ ስብ የያዘ ምግብ፤ በገላጭ ጽሁፉ ላይ በሃይድሮጅኔሽን ሂደት ያለፈ መሆኑ መግለጽ አለበት፡፡
4) ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ-ነገር የያዘ ምግብ ገላጭ ጽሁፍ፤ ምግቡ ወይም በውስጡ ያለው ንጥረ-ነገር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የጤና ጠቀሜታ እንዳለው፣ ጥንካሬ እንደሚሰጥ፣ ጥራት ያለው ወይም ተመሳሳይ አገላለጽ በመጠቀም በተለይም እንደ “ምርጥ”፣ “ጥራት ያለው”፣ “ፕሪሚየም”፣ “እውነተኛ”፣ “ኦሪጂናል” በሚል አገላለጽ ምግቡ ጠቀሜታ ወይም ጥራት እንዳለው መግለጽ የተከለከለ ነው፡፡

5) ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብ ንጥረ ነገር ያለው ምግብ የካርቱን፣ አኒሜሽን፣ የአኒሜሽን ገጸ ባህሪያት፣ ልጆችን የሚስብ ታዋቂ ገጸ-ባህሪን፣ የልጆች ሙዚቃን ወይም ድምጽን፣ የልጆች አገላለጽን ወይም ቋንቋን፣ የልጆች ስዕል ወይም ፎቶ፣ በገላጭ ጽሑፉ ላይ እንዲኖረው ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

6) የምርቱ መጠን አነስተኛ በመሆኑ ተቀዳሚ ማሸጊያ የገላጭ ጽሁፍ ለመጻፍ የማያስችል እንደሆነ ገላጭ ጽሑፍ በሁለተኛ ማሸጊያ ላይ ሊቀመጥ ይችላል፤ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 7. የምግብ ንጥረ ነገር መግለጫ

1) ማንኛዉም ምግብ በተቀዳሚ ማሸጊያው ላይ ምግቡ የያዘዉን የምግብ ንጥረ-ነገሮች እና መጠናቸዉን የሚያሳይ የምግብ ንጥረ ነገር መግለጫ መያዝ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት በምግቡ ላይ የሚደረግ የንጥረ-ነገር መግለጫ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡

ሀ) አጠቃላይ የኃይል መጠን፤

ለ) አጠቃላይ ካርቦሃይድሬትስ፣ አጠቃላይ ስኳር፣ ምግብ በማምረት ሂደት በምግቡ ዉስጥ በተናጠል የተጨመረ ስኳር እና የጨው ወይም ሶዲየም መጠን፤

ሐ) አጠቃላይ የስብ፣ ሳቹሬትድ ስብ፣ በፋብሪካ ሂደት የተለወጠ ስብ መጠን፤

መ) በባለስልጣኑ የሚወሰን ሌላ ንጥረ ነገር መረጃ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚገለጹት የምግብ ንጥረ ነገሮች ዝርዝር የምግብ ንጥረ-ነገሮቹ በ100 ግራም ወይም ሚሊ ሊትር ባላቸዉ መጠን ቅደም ተከተል ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ይሆናል፡፡

## 8. የጤና ማስጠንቀቂያ ገላጭ ጽሁፍ

1) ማኛዉም ሰዉ በዚህ አንቀጽ የተመለከተዉን የጤና ማስጠንቀቂያ ያልያዘ ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ማንኛውም ምግብን ማምረት፣ ማስመጣት፣ማከፋፈል፣ መቸርቸር ወይም ለህብረተሰብ አገልግሎት ማቅረብ የለበትም፡፡

2) ማንኛውም ምግብ በውስጡ የያዘው ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብ ንጥረ ነገር መጠን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ (1) ከተገለጸው መጠን በላይ የያዘ እንደሆነ፤ እንደያዘው የምግብ ንጥረ ነገር ዓይነት ገላጭ ጽሁፉ እንደሚከተለዉ የጤና ማስጠንቀቂያ መያዝ አለበት፤

ሀ) ከመጠን ያለፈ ሳቹሬትድ ስብ ያለዉ ከሆነ "ከመጠን ያለፈሳቹሬትድ ስብ ያለዉ"፤

ለ) ከመጠን ያለፈ ስኳር ያለዉ ከሆነ "ከመጠን ያለፈ ስኳር ያለዉ"፤ እና

ሐ) ከመጠን ያለፈ ጨዉ ያለዉ ከሆነ "ከመጠን ያለፈ ጨዉ ያለዉ"፤

መ) ከመጠን ያለፈ ሶዲየም ብቻውን ያለዉ ከሆነ "ከመጠን ያለፈ ጨዉ ያለዉ"፡፡

3) ማንኛውም ምግብ ከአንድ በላይ ቁጥጥር የሚደረግበትን ንጥረ-ምግብ የያዘ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) በተገለጸው አግባብ ለያዛቸው ንጥረ-ምግቦች ተፈጻሚ የሆኑትን ጤና ማስጠንቀቂያዎችን ሁሉ መያዝ አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተገለጸው የጤና ማስጠንቀቂያ በምግቡ ተቀዳሚ ማሸጊያ የፊት ገጽ ላይ ሶስት ማዕዘን ቅርጽ ባለው ምልክት ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (3) መሰረት የሚቀመጠው ሶስት ማዕዘን ዙሪያዉ በነጭ ቀለም መስመር የተከበበ ሆኖ መደቡ ጥቁር ቀለም እና የጤና ማስጠንቀቂያ መልዕክቱ በነጭ ቀለም የሚጻፍ ይሆናል፤ ከሶስት ማዕዘን ምልክቱ

የታችኛዉ መስመር ትይዩ መደቡ ነጭ ሆኖ በጥቁር ቀለም የተጻፈ "ጤና ሚኒስቴር ኢትዮጵያ" የሚል ጽሑፍ በውስጡ የያዘ አራት ማዕዘን መቀመጥ አለበት።

6) ማንኛውም ምግብ በውስጡ በማንኛዉም መጠን፡

ሀ) ስኳር ያልሆነ ማጣፈጫ ያለዉ ከሆነ "ስኳር ያልሆነ ማጣፈጫ ያለዉ"፤

ለ) ካፊን ያለዉ ከሆነ "ካፊን ያለዉ"፤

የሚል ጽሁፍ በተቀዳሚው ማሸጊያ ላይ መግለጽ አለበት።

7) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚጠየቅ የጤና ማስጠንቀቂያ በምግቡ ተቀዳሚ ማሸጊያ ወይም በመመሪያ በሚፈቀድ ጊዜ በሁለተኛ ወይም ሶስተኛ ማሸጊያ ላይ በሚታይ፣ በሚነበብ፣ በቀላሉ ሊጠፉ ወይም ሊለቅ በማይችል ሁኔታ መቀመጥ አለበት።

8) የጤና ማስጠንቀቂያ ምልክቱ አቀማመጥ፣ መያዝ ያለበት ስፋት፥ አጻጻፍ እና ተያያዥ ጉዳዮች ሁኔታ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## ክፍል ሦስት

## ማስታወቂያ፣ ፕሮሞሽን፣ ስፖንሰርሺፕ እና ግብይት

### 9. ስለማስታወቂያ

1) ማንኛውም ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ-ነገር የያዘ ምግብን የንግድ ስም፣ አርማ፣ የንግድ ምልክት ወይም ዓላማ በብሮድካስት፣ በቢልቦርድ፣ አጭር መልዕክት፣ በማህበራዊ ሜዲያ፣ ጋዜጣ፣ መጽሄት ወይም መሰል መንገዶች በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ማስተዋወቅ የተከለከለ ነዉ።

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ቁጥጥር የሚደርግበት የምግብ ንጥረ-ነገር ያለዉ ምግብ አምራች፣ አስመጭ፣ አከፋፋይ፣ ሻጭ ወይም ከእነዚህ አንዱን በሚወክል ሌላ ሰዉ የተደረገ የገንዘብ ወይም የዓይነት ክፍያ ሳይኖር ምርቱን መጠቀም በተመለከተ እዉነተኛ፣ ሳይነሳዊ፣ ማህበራዊ ወይም ፖለቲካዊ አስተያየት መስጠት ወይም ማቅረብ የተከለከለ አይደለም።

3) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ቢኖርም ቁጥጥር የሚደርግበት የምግብ ንጥረ-ነገር ያለዉ ምግብ አምራች፣ አስመጭ፣ አከፋፋይ፣ ሻጭ ወይም ከእነዚህ አንዱን በሚወክል ሌላ ሰዉ የተደረገ የገንዘብ ወይም የዓይነት ክፍያ ሳይኖር በመገናኛ ብዙሃን ላይ ምርቱን መጠቀም በተመለከተ በአጋጣሚ ወይም በታሪካዊ እዉነታ ወይም ምክንያታዊ በሆነ የጋዜጠኝነት ወይም የስነ-ጥበብ ስራ ወይም ትምህርታዊ ለሆነ አላማ የሚደረግ ገለጻ እንደማስታወቂያ አይቆጠርም ።

4) ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ-ነገር የያዘ ምግብ የሚያመርት፣ የሚያስመጣ ወይም የሚያከፋፍል ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አዋጅ ቁጥጥር የማይደረግበትን ሌላ ምርት ሲያስተዋዉቅ ቁጥጥር የሚደረግበት ምርትን በስም፣በዓርማ ወይም በሌላ መለያ በማያስተዋዉቅ መንገድ መሆን አለበት።

5) ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ-ነገር የያዘ ምግብ በተፈቀደ የማስታወቂያ መንገድ ሲተዋወቅ ምርቱ ለጤና ጠቃሚ እንደሆነ ወይም ምርቱ ጠቃሚ የምግብ ንጥረ-ነገር እንዳለዉ በማንኛዉም መንገድ መግለጽ የተከለከለ ነዉ።

### 10. ፕሮሞሽን እና ስፖንሰርሺፕ

1) ማንኛውም ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ-ነገር የያዘ ምግብ ጋር በተያያዘ፡-

ሀ) ምግቡን ወይም የምርቱን ንግድ ምልክት፣ መለያ ወይም ስያሜ የያዘ ሌላ ማንኛዉንም ምርት በነጻ ለተጠቃሚ መስጠት፤

ለ) ሽልማት መስጠት፣ የእጣ ወይም የሎተሪ ስልት በመጠቀም ምርቱን ወይም ገንዘብ ወይም ቁስ እንደሚያገኝ አድርጎ መግለጽ ወይም መተግበር፣

ሐ) የዋጋ ቅናሽ እንዳለ መግለጽ፣

መ) አንድ አገልግሎት ለተጠቀመ ወይም ምርት ለገዛ ምርቱን በጭማሪነት የመስጠት ወይም ለአገልግሎቱ ወይም ምርት ክፍያ መፈጸም፣

ሠ) አሻንጉሊት፣መጫወቻ፣ ካርቱን፣ አኒሜሽን፣ የልጆች ሙዚቃ ወይም ድምጽ፣ የልጆች ስዕል ወይም ፎቶ፣ ወይም ልጆችን ሊስብ የሚችል ማንኛዉም እቃ ከምርቱ ጋር በማያያዝ መስጠት ወይም መሸጥ፣

የተከለከለ ነው።

2) ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ-ነገር የያዘ ምግብ የሚያመርት፣ የሚያስመጣ፣ የሚያከፋፍል ወይም ከእነዚህ አንዱን የወከለ ማንኛውም ሰዉ እድሚያቸዉ ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ሰዎች እንዲሁም ለመዋለ ህጻናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚዘጋጅ ኩነትን፣ የጤና ተቋምን ወይም በጤና ተቋም የሚዘጋጅ ኩነትን ስፖንሰር ማድረግ አይችልም።

3) ቁጥጥር የሚደረግበት የምግብ ንጥረ-ነገር የያዘ ምግብ የሚሸጥ ሰዉ ህጻናት ምግቡን በቀላሉ በሚደርሱበት፣ በግልጽ በሚታይ እና ክፍያ በሚፈጸምባቸዉ ቦታዎች እንዲቀመጥ ማድረግ የለበትም።

4) ማስታወቂያ፣ ፕሮሞሽን እና ስፖንሰርሽፕ በተመለከተ ተጨማሪ ገደቦችን እና ክልከላዎችን ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ሊወስን ይችላል።

## 11. ሽያጭ

1) ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ-ነገር የያዘ ምግብ በዚህ አዋጅ የሚጠየቅን የጤና ማስጠንቀቂያ የሌለው ወይም የጤና ማስጠንቀቂያው የማይታይ፣ የማይነበብ፣ ያለው ምግብ መሸጥ ወይም ለሽያጭ ማቅረብ የተከለከለ ነዉ።

2) ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ-ነገር የያዘ ምግብን፤ በመዋዕለ ህጻናት፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ህጻናት ማቆያ፣ በህጻናት መዝናኛ ቦታ፣ በግልና በመንግስት የጤና ተቋማት ግቢ ዉስጥአውቶማቲክ መሸጫ ማሽንን ጨምሮ በማንኛዉም መንገድ በመጠቀም እና ከግቢው ውጭ 50 ሜትር ዙሪያ መሸጥ የተከለከለ ነው።

## 12. የምገባ አገልግሎት

1) የምገባ አገልግሎት የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ ነገርን የያዘ ምግብን ለአገልግሎት ማቅረብ አይችልም።

2) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም «የምገባ አገልግሎት» ማለት ምግብን በማዘጋጀት ለተማሪዎች፣ ለአረጋዉያን፣ ለታካሚዎች፣ ለታራሚዎች ወይም መሰል አገልግሎት መንግስት ወይም ሌላ ተቋም ምግብን በዘላቂነት የሚያቀርብበት ተግባር ነው።

## 13. የመንግስት የምግብ ግዥ

1) ማንኛውም የመንግስት አካል ቁጥጥር የሚደረግበትን ንጥረ ነገር የያዘ ምግብን መግዛት ወይም ለአገልግሎት ማቅረብ አይችልም።

2) የመንግስት የምግብ ግዢ የሚያከናውን ማንኛውም ሰው ምግቡ በዚህ አዋጅ ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ ነገር ያልያዘ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

3) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 ቢኖርም ለአስቸኳይ አደጋ ምላሽ አስፈላጊ ሲሆን ለዚያ አገልግሎት የሚዉል ብቻ ግዥ ሊፈጽም ይችላል። የዚህ ንዑስ አንቀጽ አፈጻጸም ገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣዉ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## 14. ሰብአዊ ድጋፍ

1) ማንኛዉም ሰዉ ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ምግብ በእርዳታ መስጠት አይችልም።

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ቢኖርም አስቸኳይ ምላሽ የሚፈልግ የሰው ሰራሽ ወይም የተፈጥር አደጋ ወቅት ማንኛውም ሰው ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ምግብ በእርዳታ መስጠት ይችላል።

3) ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረነገር የያዘ ምግብ የሚያመርት፣ የሚያስመጣ፣ የሚያከፋፍል ወይም ከእነዚህ አንዱን የሚወክል ሰዉ ለሰብዓዊ እርዳታ የገንዘብ ወይም የቁስ ስጦታ ማድረግ ይቻላል፤ ሆኖም የድርጅቱን ስም ከመግለጽ ባለፈ ምርቱን ማስተዋወቅም ሆነ ስለምርቱ ገለጻ ማድረግ የተከለከለ ነው።

## 15. የጥቅም ግጭት ስለመከላከል

1) ማንኛዉም ይህን አዋጅ የሚያስፈጽም የመንግስት ሰራተኛ ወይም የተቋም ሀላፊ ቁጥጥር የሚደረግበትን ምርት ከሚያመርት፣ ከሚያስመጣ፣ ከሚያከፋፍል፣ከሚልክ እና ከሚቸረችር ሰዉ ጋር የሚያደርገዉ ግንኙነት ከጥቅም ግጭት ነጻ መሆን አለበት፡፡

2) ማንኛዉም ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ምግብን የሚያመርት፣የሚያስመጣ፣የሚያከፋፍል ሰዉ ይህን አዋጅ ከሚያስፈጽም ከመንግስት አካል ጋር የሚደርገዉ ግንኙነት ቁጥጥርን ለማሳለጥ፣ግልጸኝነት ያለበት እና በሰነድ የተያዘ መሆን አለበት፡፡

3) ይህን አዋጅ የሚያስፈጽም ተቋም ውስጥ የሚሰራ የመንግስት ተሿሚ ወይም የመንግስት ሰራተኛ የምግብ ላኪን ጨምሮ ከማንኛዉም የምግብ ኢንዱስትሪ የገንዘብም ሆነ የዓይነት ስጦታ መቀበል፣ በምግብ ኢንዱስትሪው በተዘጋጀ ስልጠና፣ አውደ ጥናት፣ ሴሚናር፣ ምርምሮች ወይም መሰል ክንውኖች ላይ ለመሳተፍ አይችልም።

4) ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም ‘የሚያስፈጽም የመንግስት አካል” ማለት ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ህጎችን ተግባራዊነት የሚቆጣጠር፣ እርምጃ የሚወስድ፣ መስፈርት የሚያዘጋጅ ወይም ፈቃድ የሚሰጥ በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚገኝ የመንግስት አካል ነው።

# ክፍል አራት
# አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣት

## 16. አስተዳደራዊ እርምጃ ስርዓት

1) ባለስልጣኑ ወይም የክልል ጤና ተቆጣጣሪ ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጣውን ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ ጥሰት የፈጸመ ሰው ላይ አግባብነት ያለውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል።

2) ባለስልጣኑ ወይም የክልል ጤና ተቆጣጣሪ የሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ እንደ ጥፋቱ ዓይነት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ የገበያ ፍቃድ፣ የብቃት ማረጋገጫ ወይም የማስገቢያ ፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝ፣ ምርት መያዝ፣ ማገድ፣ መውረስና ማስወገድ፣ ምርቱ ወደ መጣበት አገር እንዲመለስ ማድረግ እና የገንዘብ መቀጮ መጣል ይሆናል።

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) የተጠቀሱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ዝርዝርና የአወሳሰድ ሁኔታ በባለስልጣኑ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

### 17. አስተዳደራዊ የገንዘብ መቀጮ

ባለስልጣኑ ወይም የክልል ጤና ተቆጣጣሪ ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጣውን ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ ጥሰት የፈጸመ ሰው ላይ ከሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ ወይም ለብቻው የገንዘብ መቀጮ እንደሚከተለው ለመጣል ይችላል።

1) የብቃት ማረጋገጫ ወይም የማስገቢያ ፈቃድ ማገድ ከብር 5,000-100,000
2) የብቃት ማረጋገጫ ወይም የማስገቢያ ፈቃድ መሰረዝ ከብር 10,000-150,000
3) ምርት መውረስ፣ ከገበያ እንዲሰበሰብ ማድረግ፣ ምርት ማገድ፣ ወይም ከንኡስ አንቀጽ 1-3 የጥፋት ዓይነቶች ውስጥ ያልተካተተ ሲሆን ከ3,000-50,000።
4) ዝርዝሩ ባለስልጣኑ በሚያወጣ መመሪያ የሚወሰን ሆኖ የጥፋቱ ሁኔታ ከፍያል በተለይም ምርቱ ወይም ማስታወቂያው በስፋት የተሰራጨ እንደሆነ ቅጣቱ ከድርጅቱ ዓመታዊ የተጣራ ትርፉ እስከ 10% የሚደርስ ሊሆን ይችላል።

### 18. የወንጀል ቅጣት

1) ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት የሚጠየቅን የጤና ማስጠንቀቂያ መያዝ ያለበት ምግብን የጤና ማስጠንቀቂያ ሳይኖረው ወይም የጤና ማስጠንቀቂያ መስፈርትን ሳያሟላ ያመረተ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ ያከማቸ፣ ያከፋፈለ፣ ወይም በችርቻሮ የሸጠ ወይም ለአገልግሎት ያሰራጨ ወይም ያቀረበ እንደሆነ ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር አስር ሺህ በማያንስ ከብር ሁለት መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።
2) ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ የተከለከለ የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ምግብ ያመረተ፣ ወደ አገር ውስጥ ያስገባ፣ ያከማቸ፣ ያከፋፈለ፣ ወይም በችርቻሮ የሸጠ ወይም ለአገልግሎት ያሰራጨ ወይም ያቀረበ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማያንስ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር አስር ሺህ በማያንስ ከብር ሁለት መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።
3) በሙስና ወንጀል የተመለከቱ የወንጀል ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 የተደነገገዉን የተላለፈ እስከ ሶስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ በማይንስ ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።
4) ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያ የተቀመጠን የማስታወቂያ፣ የፕሮሞሽን እና የስፖንሰርሺፕ፣ እርዳታ፣ የመንግስት ግዢ ክልከላ ወይም ገደብ የተመለከቱ ድንጋጌዎች የተላለፈ እንደሆነ ከሶስት ወር እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከብር አስር ሺህ በማያኝስ ከሁለት መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።
5) ማንኛውም ሰው ቁጥጥር የሚደረግበትን የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ምግብ በተከለከለበት ቦታ የሸጠ ወይም በመንገድ ላይ በአውቶማቲክ ማሽን ሽያጭ ያከናወነ እንደሆነ ከሶስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ በማያንስ ከሃያ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።
6) ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ከንኡስ አንቀጽ (1) እስከ (3) ከተመለከቱት አንዱን የወንጀል ተግባር በቸልተኝነት የፈጸመ እንደሆነ እንደ ነገሩ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከአስር ሺህ በማያንስ ወይም ከሃምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

7) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1-6 የተመለከተው የወንጀል ድርጊት የተፈጸመው የህግ ሰውነት ባለው ድርጅት እንደሆነ፤ ከድርጅቱ የተጣራ ዓመታዊ ትርፍ ከአስር በመቶከማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

8) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (7) መሰረት ከሚወሰነው መቀጮ በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ እንዳግባብነቱ ድርጅቱ በተመሳሳይ ስራ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለዘለቄታው እንዳይሳተፍ ሊከለክል ይችላል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 19. የምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ተፈጻሚነት

በዚህ አዋጅ ቁጥጥር የሚደረግበት ምግብ በምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 እና የአዋጁ ማስፈጸሚያ ደንብና መመሪያ ስለምግብ አስተዳደርና ቁጥጥርን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

### 20. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

2) ባለስልጣኑ ይህንን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የወጣውን ደንብ ለማፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

### 21. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ከታወጀበት ቀን ጀምሮ ባለዉ አሥራ ሁለተኛዉ ወር የመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

**ታዬ አጽቀስላሴ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**